# ከፋኝ የኢትዮጵያ አንድነት ንቅናቄ (ከኢአን)

## የተሰጠ መግለጫ

ህወሀት እያራመደ ያለው ታላቋን ትግራይ የመመስረት ዓላማ ለማሳካት ፍጹም አምባገነናዊ በሆነ መንገድ ምርጫ ቦርድ፤የህግ አውጭ አካላትን፤ህግ ተርጓሚና ህግ አስፈጻሚ ተቋማትን በበላይነት ተቆጣጥሯል።ሐገራችን ኢትዮጵያ ከአንድ ብሔር በመጡ የህወሀት አመራር ስር በመውደቋ የተለያዩ አመለካከቶችና ሀሳቦች ለውይይት የማይቀርቡበት ሀሳብን በነጻነት መናገርና መጻፍ የማይቻልበት፤ የፍትህ የመብትና የዴሞክራሲ ጥያቄ ማቅረብ በሽብርተኝነት የሚያስከስስበት ሐገር ሆናለች።

በመሆኑም አምባገነኑ ህወሀት በሁሉም ክፍሎች የተነሳውን ሰላማዊ የመብት ጥያቄ ለማፈን ወጣቱን በመግደል በማሰርና ከሀገራቸው እንዲሰደዱ በማድረግ ላይ ይገኛል።

ህወሀት ከበረሀ ይዞት የመጣውን ድብቅ አጀንዳ በግልጽ በማውጣት በመንቀሳቀሱ ምክንያት የኢትዮጵያ ህዝብ የህወሀትን አገዛዝ በመቃዎም በተደራጀም ባልተደራጀም በሰላማዊም በትጥቅም ህወሀትን ለመታገል በርካታ ሙከራዎች ተደርገዋል እየተደረጉም ይገኛሉ።

ይሁን እንጅ ትግሉ በአግባቡ የተደራጀና የተቀናጀ ባለመሆኑ ዳር ሊደርስ አልቻለም። ይልቁንም ለዜጎቹ ግድ የለለው ወያኔ የሚደረጉ የትግል እንቅስቃሴዎችን በመነሻነት በመጠቀም ለመግደል ለማሰርና ለማሳደድ የመጠቀሚያ አጀንዳ አድርጎት ይገኛል። ቢሆንም የወያኔ ግፍ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየባሰ እንጅ እየተስተካከለ የሚሄድ ባለመሆኑ የሀገራችን ህዝብ ብሶት አንገፍግፎት ወያኔን በመታገል ከጫፍ እስከ ጫፍ በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል።

የህወሀት ቡድን የክልሉን ስልጣንና ተግባር ቸል በማለት በኮማንድ ፖስት ስም የየክልሉን የጸጥታና የደህንነት ሐይል የመከላከያ ሐይል እንዲከበው በማድረግ የፖለቲካና የጸጥታ አመራር ስልጣን በሙሉ በህወሀት እጅ እንዲወድቅ አድርጓል።

በመሆኑም አሁን በሀገራችን ያለው የፖለቲካ ሁኔታ በዝምታ የሚታለፍበት ደረጃ ላይ ባለመሆኑ ወያኔ በዚህ ግራ በተጋባ ሁኔታ ላይ

ባለበት ሆኖ እያለ ቀርቶ ሰላማዊ ንኝ ብሎ ባሰበበት ወቅት እንኳን ችግሮቹን መፍቻ አማራጭ ብሎ የሚወስደው እስርንና ጅምላ ጭፍጨፋን ነው።

በመሆኑም ምርጫችን ጠባብና በአስገዳጅ ሁኔታ ውስጥ ሆነን የሚወሰን ነው ይሄውም፡-

1. እጅን አጣጥፎ በመቀመጥ የወያኔ የግድያ ሰለባ መሆንና
2. ከከተማ ወደገጠር በመውጣት ወያኔን በአፈሙዝ መፋለም ናቸው

ምርጫዎቹ ተተኪና አማራጭ የሌላቸው በመሆኑ ለአንዱ መሰለፍ ግድ ይላል ምክንያቱም ሰላማዊ የትግል ስልትና ለውጥ በወያኔ በኩል ዝግ በመሆኑና ብዙ ሰላማዊ ለውጥ አራማጆችን ለግድያ እስርና ስደት የዳረገ ስለሆነ።

ከላይ ከቀረቡት አማራጮች ሁለተኛውና ታሪካዊ የሚያሰኘውን ምርጫ መምረጥ የሁሉም ኢትዮጵያዊ ፍላጎት ቢሆንም ለጊዜው በዚህ ምርጫ አምነው ተግባራዊ ለማድረግ ቤታቸውን ወደ ኋላ ትተው ጫካ የወጡ ቁርጠኛ የኢትዮጵያ ልጆች ጥቂት አይደሉም። አሁን ባለው የኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ተከታዮቻቸው እልፍ አእላፍ እደሆኑ እሙን ነው።

በመሆኑም አሁን ያለውን የተነቃቃ የህዝብ ትግል ቅርጽ በማስያዝ በታጠቀና በተደራጀ መልኩ ግለቱን የጠበቀ የትግል ጉዞ መምራት ይቻል ዘንድ

ቦርቀው ካልጠገቡ ለጋ ህጻናት እስከ እድሜ ጠገብ አረጋውያን በቤት፣ በት/ቤት፣ በገበያ፣ በእምነት ተቋማት፣ ያለርህራሄ መትረየስ የሚያርከፈክፍን አረመኔ ዘረኛ ድርጅትን ማስወገድ አይነተኛው መንገድ ነው።

የእናት፣የአባት፣የእህት፣የወንድም፣የልጅ፣የጓደኛ በግፍ የፈሰሰ ደምን እንዲሁም በየጥሻው በወያኔ ቅልብ ሃይል ጥፍራቸው እየተነቀለ በቁርና ሀሩር አሳርን እያዩ ያሉ ወገኖቻችን ሰቆቃ ለመርሳት መሞከር ወይንም በዝምታ ማለፍ ኢትዮጵያዊ ማንነታችን አይደለምና በወያኔ ስናይፐር በከንቱ ከማለፍ የትግሉ አጋር በመሆን የወያኔን ቀብር ለማፋጠን ትግሉን እንድትቀላቀል/ይ ከፋኝ የኢትዮጵያ አንድነት ንቅናቄ ጥሪዉን ያስተላልፋል።

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ



**ኢትዮጵያ ለዘላለም በክብር ትኑር!!**